# በመንደር መሰባሰባችን…

## ክፍል አንድ

**ሰለሞን ተስፋዬ 07-03-14**

ወይዘሮ ሐሲና ሙሐመድ የ50 ዓመት አዛውንት ናቸው። ነዋሪነታቸው በአዋሽ አርባ ፈንታሌ ወረዳ በቀበና ቀበሌ ነው። በአካባቢው የከሰም ስኳር ልማት ፕሮጀክት ግንባታ ሲጀመር በርካታ የተምታቱ ሐሳቦች ይሰነዘሩ ስለነበር መደናገራቸው አልቀረም። መንግሥት ልማቱን አስመልክቶ ይለው የነበረውን ለማመን ህዝቡ የተቸገረበት ጊዜ እንደነበር ይናገራሉ። “ከአባቶቻችንና ከአያቶቻችን የወረስነውንና ሕይወትን እንመራበት የነበረውን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ እየተዘዋወሩ ቋሚ መኖሪያ መንደር ሳይኖር የከብት ጭራ በመከተል ህይወትን በመንከራተት እንገፋ ነበር“ ይላሉ።

ከዚህ የተነሳ የከሰም የስኳር ልማት ፕሮጀክት ሲጀመር በመስተዳድሩ በመንደር እንድንሰፍር ስንጠየቅ ያቅማሙ በርካቶች ናቸው፡፡ ማግኘት የምንችለውን ጥቅም አሻግረን ማየት የቻልንበት ሁኔታ አልነበረም። ይልቁንም በአካባቢው አንዳንድ ፀረ ሠላም ኃይሎች የሚያናፍሱትን የተለያየ ወሬ እየሰማን የመደናገር ሁኔታ ተፈጥሮብን ነበር። መንግሥት በተደጋጋሚ ያደረገውን ቅስቀሳና የልማት ጥሪ ቀድመው የተረዱ በፕሮግራሙ ተሳታፊ እየሆኑና ለሌላው ኅብረተሰብ ስለ ልማቱ ጠቀሜታ እያስረዱ የስኳር ልማት ፕሮጀክቱ ተጀመረ“ ይላሉ ወይዘሮ ሐሲና።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ቁጥራቸው ቀላል የማይባል የአካባቢው ነዋሪዎች በመንደር እንዲሰፍሩ ሲደረግ እኔም እድሉ ገጠመኝ። እኔ ብቻ ሳልሆን በአፋር ክልል በአዋሽ ፈንታሌ ወረዳ በሣቡሬ፣ ቀበና፣ ደሆና ቦሎይታ ቀበሌ ነዋሪዎች ከከሰም የስኳር ልማት ፕሮጀክት ተጠቃሚ መሆን ችለዋል፤ ዛሬ ገቢያችንም አድጓል፤ የማህበራዊ አገልግሎት ተጠቃሚም ሆነናል ይላሉ ወይዘሮ ሐሲና።

በመንደር የመሰባሰቡን ፕሮግራም እንድንቃወም በርካታ ፀረ ልማት ኃይሎች ሊያደናግሩን ጥረት ያደርጉ ነበር። ይሁንና ከአካባቢው አስተዳደርና ከስኳር ኮርፖሬሽን የሥራ ኃላፊዎች ጋር በተደረጉ ተከታታይ የግንዛቤ ማስፋፊያ መድረኮች ምክንያት በመንደር መሰባሰቡ ከማንም ይልቅ የሚጠቅመው እኛኑ መሆኑን መገንዘብ ቻልን፡፡ በመሆኑም በፈቃዳችን እየተመዘገብን በአዳዲስ መንደሮች ሰፈርን። በሰፈርንባቸው አዳዲስ መንደሮች ውስጥ በርካታ ጠቃሚ ነገሮችን ማግኘት ችለናል። ልጆቻችን የትምህርት ዕድል፤ ሴቶች በአካባቢው የወፍጮ አገልግሎት፤ ሕጻኑም ሆነ አዋቂ የሕክምና አገልግሎት ማግኘት ችሏል ብለዋል።

ወይዘሮ ሐሲና አያይዘውም በተሰባሰብንበት መንደር የጤና ኬላ በመገንባቱ የእናቶችንና የሕጻናትን ሞት መታደግ ችሏል። እናቶች  በጤና ባለሙያዎች እርዳታ እንዲወልዱ እየተደረገ ነው። በመንደራችን የሚሰጠው የወፍጮ አገልግሎትም  የሴቶችን የሥራ ጫና እንዲቀንስ አግዟል። በመንደር መሰባሰባችን ከነበርንበት የጨለማ ህይወት ወጥተን በብርሃን እንድንጓዝ አስችሎናል ሲሉ ይናገራሉ፡፡

የአካባቢው ነዋሪዎችም የወይዘሮ ሐሲናን ሐሳብ ይጋራሉ። በደሆ ቀበሌ ነዋሪ አቶ አሊ አሙድ አሲ፣ የማቡሬ ቀበሌ ነዋሪው ወጣት በልአ ሰያሌና የቦሎይታ ቀበሌ ነዋሪ አቶ ኡዳ ኡመት በየበኩላቸው የከሰም ስኳር ልማት ፕሮጀክት የአካባቢውን ኅብረተሰብ አኗኗር መቀየር የቻለ የሕዝብ አለኝታ በማለት ይገልፁታል።

በመንደር በመሰባሰባችን ትምህርት ቤት፣ የሕክምና ተቋም፣ የእንስሳት የሕክምና አገልግሎት፣  የኤሌክትሪክ ኃይል፣ ንጹህ የመጠጥ ውኃ፣ መስኖ ገብ ማሣ፣ የወፍጮ  አገልግሎትና ቋሚ የእምነት ተቋማት ተገንብተው አገልግሎት እየሰጡ በመሆኑ ቀደም ሲል የነበረን የተበታተነና ለችግር የተጋለጠ ሁኔታ ተለውጦ አኗኗራችን ተሻሽሏል ብለዋል። በቀደሙት ሥርዓታት የአካባቢው አርብቶ አደር ትኩረት በመነፈጉ ኑሮው  በባህላዊ የከብት ዕርባታ ላይ የተመሠረተ ነበር። ብቸኛ አንጡራ ሀብቶቹም ከብቶቹ በመሆናቸው የከብቶቹን ሕይወት ለመታደግ ወቅት

በተፈራረቀ ቁጥር ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ቤተሰቦቹን አስከትሎ በመዘዋወርና ጊዚያዊ ማረፊያ ጎጆ በመቀለስ ለመኖር ይገደድ ነበር።

ይህንኑ ባህላዊ የከብት እርባታ ሥራን በተሻለ መንገድ ለማካሄድ እንኳን የምክር አገልግሎት የሚያገኝበት ሁኔታ አልነበረም። በአካባቢው የእንስሳት ሕክምና ሆነ ባለሙያ ባለመኖሩ የተነሳም ከብቶቹ በበሽታ ይጠቁ ነበር። አንድ አርብቶ አደር በርካታ ከብቶች ካራባ በኋላ ሳይታሰብ በድንገት በሚከሰት የከብት በሽታ ለዓመታት የደከመበትን ሐብት በአንዴው ያጣል። ከስኳር ልማት ፕሮጀክቱ ጋር ተያይዞ በመጣ ለውጥና ከዚያም ባሻገር መንግሥት የአርብቶ አደሩን ሕይወት ለመቀየር ነድፎ በመተግበር ላይ ባለው ፖሊሲና ስትራቴጂ ምክንያት የአርብቶ አደሩ ሕይወት በተጨባጭ እየተለወጠ ነው።

የአርብቶ አደሩን ሕይወት ለመቀየር በሚደረገው ጥረት ቀዳሚው ነገር አርብቶ አደሩ የተረጋጋ ሕይወት እንዲኖረው የሚያግዝ የራሴ የሚለው ቋሚ መንደር ሲኖረው ነው። በዘላቂነት አርብቶ አደሩን በፈቃዱ በመንደር የማሰባሰብ ሥራ ማከናወን ዋናው መፍትሄ ነው፤ ይህ እውን እስኪሆን ድረስ ሳይጠበቅ አርብቶ አደሩ ባለበት ሁኔታ ተጠቃሚ ለማድረግ የሚቻልበት አሠራር በመፍጠር ተንቀሳቃሽ የትምህርትና የሕክምና አገልግሎት በየአካባቢ እንዲኖር መንግሥት እየሰራ ይገኛል።

የሰውና የከብት የህክምና አገልግሎት በተንቀሳቀሽ መልክ በማቋቋም አርብቶ አደሩን ለመታደግ ቆርጦ የተነሳው የኢትዮጵያ መንግሥት ባለፉት አሥር ዓመታት ቀላል የማይባል ለውጥ በአኗኗራቸው ላይ ማምጣት ችሏል። በተለይ ደግሞ በአካባቢው የተለያዩ ትላልቅ የልማት ፕሮጀክቶች እንዲቋቋሙ በማድረግ ኅብረተሰቡን ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉ በተግባር እየታየ መጥቷል።

ለእያንዳንዱ ቤተሰብ አንድ ሄክታር መስኖ ገብ መሬት ተሰጥቷል። አርብቶ አደሩ የተፈጥሮ ዝናብን ሳይጠብቅ በዓመት ሁለትና ሦስት ጊዜ ማምረት ችሏል። ከእንስሳት እርባታው ጎን ለጎን የተለያዩ ሰብሎችን ማምረት የቻለበት ሁኔታ

ተፈጥሯል። እነዚህን ሰብሎችና ሌሎች እንደ ቲማቲም፣ ድንች፣ ቃሪያና ሽንኩርት የመሳሰሉትን እያመረተ በመሸጥ ተጨማሪ ገቢ ማግኘት ችሏል።

ፋብሪካው የአካባቢውን ኅብረተሰብ የበለጠ ተጠቃሚ ለማድረግ ባወጣው እቅድ መሠረት ሸንኮራ አገዳን እያለሙ ለፋብሪካው ማቅረብ የሚፈልጉ አርብቶ አደሮችን በማስተባበርና በማህበር ተደራጅተው ሸንኮራ አገዳ እያመረቱ በማቅረብ ተጠቃሚ የሚሆኑበት አሠራር ተቀይሷል። እስካሁን ባለው ሂደት በፈቃደኝነት የተደራጁት አርብቶ አደሮች በወንጂ ስኳር ፋብሪካ ከሚገኙ አገዳ አብቃይ አርሶ አደሮች ተሞክሮ እንዲወስዱ ተደርጓል፡፡

በአዋሽ ፈንታሌ ወረዳ የሚገኙ የአራት ቀበሌ ነዋሪዎች እንደሚመሰክሩት በመንደር በመሰባሰባቸው በከፍተኛ ሁኔታ ተጠቃሚ መሆን ችለዋል። በአራቱ ቀበሌዎች ሦስት ሺህ የሚደርሱ ቤተሰቦች የጥቅሙ ተቋዳሽ ሆነዋል። በቀበሌዎቹ የማህበራዊ አገልግሎት መሥጫ ተቋማት ሙሉ በሙሉ በመገንባታቸው ኅብረተሰቡ የአገልግሎቱ ቀጥተኛ ተጠቃሚ ሆኗል።

ከዚህም በተጨማሪ በፋብሪካውም ሆነ በሸንኮራ አገዳ ማሣው ተቀጥረው የሚሰሩ በርካታ የአካባቢው ተወላጆች ይገኛሉ። በከሰም ስኳር ልማት ፕሮጀክት እስካሁን በአንደኛው ዙር በአገዳ ተክል እንዲሸፈን በተደረገው ከ5 ሺህ 500 መቶ ሄክታር መሬት በላይ ማሣ የአካባቢው ተወላጆች በተለያየ መልክ ተሳታፊና ተጠቃሚ ሆነዋል። በሁለተኛው ዙር ደግሞ በሰባት ሺህ ሄክታር መሬት ላይ የአገዳ ተከላ ይካሄዳል፡፡ አጠቃላይ በከሰም ስኳር ልማት ፕሮጀክት በ20 ሺህ ሄክታር መሬት ላይ የሸንኮራ አገዳ እንደሚለማ ታውቋል።

የከሰም ስኳር ልማት ፕሮጀክት ከአሚባራ የእርሻ ልማት ድርጅት ጋር ከስድስት ሺህ ሄክታር በላይ በሆነ መሬት አገዳ ማልማት የሚያስችል ስምምነት ተደርሷል፡፡ በአሁኑ ወቅት ከ3300 ሄክታር በላይ መሬት ላይ የሸንኮራ አገዳ እየለማ ይገኛል፡፡ የከሰም ስኳር ፋብሪካ ግንባታ ከተያዘለት ዕቅድ በላይ እየተፋጠነ ነው፤ በፕሮጀክቱ የእርሻ ዘርፍ የሥራ ዕድል ከተፈጠረላቸው ዜጎች መካከል ከ80 በመቶ በላይ የአካባቢው ነዋሪዎች ናቸው። አገሪቱ በአምስት ዓመቱ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን

እቅድ ከያዘቻቸው አሥር የስኳር ፋብሪካ ግንባታዎች መካከል አንዱ የሆነው የከሰም ስኳር ልማት ፕሮጀክት ለአካባቢው ኅብረተሰብ እያስገኘ ያለው ፋይዳ የጎላ ሆኗል።

በአፋር ብሔራዊ ክልል በአዋሽ ፈንታሌና  በዱለቻ በሚገኝ የተንጣለለ ሜዳ ላይ እየተገነባ ያለው ፕሮጀክት የአካባቢውን አርብቶ አደር ከእንስሳት እርባታ በተጨማሪ እርሻን በዘመናዊ መንገድ በማስፋፋት የተረጋጋና የተሻለ ሕይወት መምራት አስችሎታል። ከቡልጋ ተራራዎች እየመነጨ የአዋሽ ፈንታሌ ወረዳን እያቋረጠ የሚወርደውን  የከሰም ወንዝ አቁሮ ለመጠቀም የሚጠራቀመውን ውኃ ለመስኖ ልማት ለማዋል  በሚያስችል መልክ በመገንባት ላይ ያለው የከሰም ግድብ ግንባታው እየተፋጠነ ይገኛል። በዚህ ቦታ የሚገኙ ባለሙያዎች ሥራቸውን ቀን ተሌት ይሰራሉ። ደከመኝ የሚባል ነገር የለም። ሁሉም ዓላማን ሰንቀው የተጣለባቸውን ኃላፊነት ለመወጣት ደፋ ቀና ማለቱን ከተያያዙት ዓመታት ተቆጥረዋል።

የድካማቸው ፍሬም እነሆ መታየት ጀምሯል። በአሁኑ ወቅት 99 በመቶ የሚሆነው የግድቡ ግንባታ ሥራ ተጠናቋል። ሙሉ በሙሉ ሲጠናቀቅ ከግማሽ ቢሊዮን ሜትር ኪዩብ በላይ ውኃ የመያዝ አቅም ይኖረዋል። ግድቡ 720 ሜትር ስፋትና 90 ሜትር  ከፍታ አለው። እስካሁን በአገሪቱ እየተገነቡ ካሉ ተመሳሳይ የመስኖ ልማት ግድቦች በከፍታው  የመጀመሪያ  ደረጃ የመያዙን ያህል ለአካባቢው ሕብረተሰብ የሚሰጠው ጠቀሜታም በዚያ ልክ እንደሆነ ነዋሪዎች ይናገራሉ።

በግድቡ ደቡብና ሰሜን አቅጣጫዎች ቦዮች ተሰርተዋል። እነዚህን ካናሎች በመጠቀም የሚጠራቀመውን ውሃ በሁለት አቅጣጫ በማፍሰስ ከ20 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት የሸንኮራ አገዳ ለማልማት የሚያስችል አቅም ይኖረዋል። ይህ የፋብሪካውን ሸንኮራ አገዳ ማሣን ከማልማት አልፎ የአካባቢውን ማኅበረሰብ እርሻዎችን ለማልማት የሚኖረው ፋይዳ የጎላ ነው።

መንግሥት የአገሪቱን የስኳር ፍላጎት ለማሟላትና ምርቱን በማስፋት በዘርፉ የውጭ ምንዛሪን ገቢን ለማሳደግ በያዘው እቅድ መሠረት ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ መድቦ እየሰራ ይገኛል። የከሰም የስኳር ልማት ፕሮጀክትም በከፍተኛ ወጪ

እየተገነቡ ከሚገኙ የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች አንዱ ነው። ለግድቡ እስካሁን 2 ነጥብ 6 ቢሊዮን ብር ወጪ ሆኗል፡፡

ከዚህም ባሻገር የከሰም ግድብ የሥራ ልምድን ለማካበት የራሱ በጎ ጫና ማሳደሩ ይታመናል። ግንባታው እየተከናወነ ያለው በውኃ ሥራዎች ድርጅት አማካይነት በመሆኑ የአገር ውስጥ የግድብ ሥራ አቅም በሚገባ እንዲፈተሽ አግዟል። ግድቡ የኢትዮጵያውያን የምህንድስና ባለሙያዎች አቅም በተግባር ማሳደግ ከቻሉ ትላልቅ ፕሮጀክቶች አንዱ ነው።

አዋሽ ፈንታሌ ወረዳ በረሃማ አካባቢ ነው። ከዚህ ቀደም የአካባቢው ሕዝብ የሚጠቀመው የጉድጓድ ውኃን ነበር። በአካባቢው በቂ የጉድጓድ ውኃ ባለመኖሩ ኅብረተሰቡ መስኖ ገብ እርሻን ለማልማት ይቸገር ነበር። አሁን ግን ከከሰም ወንዝ ተጠልፎ የሚፈሰው የመስኖ ውኃ የፋብሪካውን የሸንኮራ አገዳ ማሣ ከማልማት ጎን ለጎን የአካባቢው ነዋሪዎች የመስኖ ውኃ እንዲያገኙ አስችሏቸዋል። ነዋሪዎቹ መሬትን በመስኖ ከማልማት ባሻገር ውኃውን ለተለያዩ አገልግሎቶች እየተጠቀመበት ይገኛል።

በዚህ በረሃማ አካባቢ የሚኖሩት የአዋሽ ፈንታሌ ወረዳ ነዋሪዎች በአካባቢው በከሰም ግድብ አማካይነት የመስኖ ሥራዎቹ በስፋት መካሄድ ከመጀመራቸው ጋር ተያይዞ የአካባቢው የአየር ፀባይ በተወሰነ ደረጃ መቀዝቀዙን ነዋሪዎቹ ይናገራሉ። በተያዘው እቅድ መሠረት ሥራዎች እየተፋጠኑ ይገኛሉ። በፕሮጀክቱ ለማልማት ከተያዘው ከ20 ሺህ ሄክታር መሬት እስካሁን ድረስ በ5500 ሄክታር ማሣ ላይ የተተከለው አገዳ ለምርት እየደረሰ ይገኛል።

አጠቃላይ ሥራው እየተፋጠነ በመሆኑ በመጀመሪያው ዙር ከ13 ሺህ ሄክታር መሬት ላይ አገዳ ተከላ ለማካሄድ ታቅዷል፡፡ በሁለተኛው ዙር ደግሞ ሰባት ሺህ ሄክታር መሬት ላይ አገዳ ለማልማት በዕቅድ መያዙን መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከዚህም በተጨማሪ እቅዱን ይበልጥ ለማሳካት የከሰም ስኳር ልማት ፕሮጀክት በአቅራቢያው ከሚገኘው የአሚባራ እርሻ ልማት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ጋር ስምምነት አድርጓል። በስምምነቱ መሠረት የአሚባራ የእርሻ ልማት በራሱ ስድስት ሺህ ሄክታር መሬት ላይ የሸንኮራ አገዳ በማልማት ለፋብሪካው

በሽያጭ ያቀርባል። እስካሁን ባለው መረጃ መሠረት በሦስት ሺህ ሄክታር መሬት ላይ የሸንኮራ አገዳ ተከላ አካሂዷል።

ፕሮጀክቱ የአካባቢው ኅብረተሰብን በተለይ በመንደር ማሰባሰብ ፕሮግራሙ የታቀፉትን የአዋሽ ፈንታሌና በዱለቻ ወረዳ የሚገኙ የሣቡሬ፣ የደሆ፣ የቦሎና የቀበና ቀበሌ ነዋሪዎችን በይበልጥ ተጠቃሚ አድርጓል፡፡ ነዋሪዎቹም አንዳንድ ሄክታር መስኖ ገብ መሬት በማግኘታቸው በአገዳ አብቃይ ማህበራትና ዩኒየኖች በመደራጀት ራሳቸውን ጠቅመው ለፋብሪካው በቂ የአገዳ ግብዓት እንዲያቀርቡ የሚያስችል የተለያየ ሙያዊ ድጋፍ እየተደረገላቸው ይገኛል።

ፕሮጀክቱ በቅርቡ አገዳ በሚተከልባቸው አዳዲስ ቦታዎች ላይ ምንጣሮና መሬትን የመደልደል ሥራዎችን በስፋት በማከናወንና በየዕለቱ የአገዳ ተከላ በማካሄድ ላይ ይገኛል። በታህሳስ 2007 ዓ.ም ሥራ ለሚጀምረው የከሰም የስኳር ፋብሪካ የአገዳ ግብዓት እጥረት እንዳይኖር የእርሻ ሥራው በተፈለገው ፍጥነት እየተከናወነ እንደሚገኝ መረጃዎች ያሳያሉ።

የአገዳ ችግኞችን ለማባዛት የሚረዱ የግሪን ሐውስ ማዕከላት ተዘጋጅተው ችግኝ የማፍላት ሥራዎች በመካሄድ ላይ ነው፡፡ ከመቀሌ ዩኒቨርስቲ በምርምር የተገኙ ምርጥ የአገዳ ዝርያዎች የአካባቢውን የአየር ፀባይና አፈር እንዲላመድ የሚያስችል ተግባራት እየተከናወኑ ነው።

በዘር ማባዣ ማዕከላቱ የችግኝ እንክብካቤ ሥራዎች በሙሉ የአፋር ተወላጅ በሆኑ ሴቶች እየተከናወነ ነው፡፡ በእርሻ ቦታው ላይ በሚካሄደው የአገዳ ተከላ ሥራ ላይ ጭምር የአፋር ሴቶች ተሳትፎ የላቀ ነው፡፡ ከእንስሳት እርባታ ጎን ለጎን ግብርና ሥራ እንዲላመዱ ያስቻለ ፕሮጀክት ሆኗል። በዚህ ምክንያትም የአካባቢው ነዋሪዎች ምጣኔ ሀብታዊ ተጠቃሚነትን አሳድጎታል።